# የእምነት ጀግኖች (12)

## ጥናት አንድ (ዕብ 11:8-10 ዘፍ 11:31-12:9)

የጥናት ዓላማ: አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሄር እንድናደርግ የሚጠይቀን ነገር ለጊዜው ባይገባንም በእግዚአብሄር ሁሉን አዋቂነት ላይ በመታመን መታዘዝ እንደሚኖርብን ለመማር::
የምናሰላስለው ጥቅስ: «...እኔ ወደማሳይህ ምድር ሂድ:: ...ስለዚህ አብራም እግዚአብሄር እንዳዘዘው ወጣ፣ ሎጥም አብሮት ሄደ::» ዘፍ 12:1, 4

1. የአብርሃም አባት ታራ ከቤተሰቡ ጋራ የሰፈረበት ምድር ምን ይባላል? ሊሄድበት ስለተነሳበት ምድርስ የምናውቀው ነገር ምንድነው?
2. በዘፍ 12:1 ላይ አብርሃም ምን እንዲያደርግ ሲጠየቅ እናገኘዋለን? አብርሃም የተጠየቀው ጥያቄ ከባድ ነው ብለህ ታምናለህ ወይ? ለምን?
3. የአብርሃምን ጥሪና ለሰዎች በወንጌል አማካኝነት በሚቀርብላቸው ጥሪ መካከል የምታየው ተመሳሳይነት አለ ወይ? አለ ካለክ በማነጻጸር አስረዳ::
4. በዕብ 11:8-9 ውስጥ አብርሃም ለእግዚአብሄር ጥሪ ስለመለሰው ምላሽ የሚጠቁመንን ነገሮች ዘርዝር
5. ዛሬ ያነበብነውን ክፍል በመመርኮዝ እግዚአብሄር ለአብርሃም የገባለት የተስፋ ቃሎች ምን ምንድናቸው?
6. የወንጌልን ጥሪ ለምንቀበለው የተገባልንን ቃልኪዳን ለአብርሃም ከተገባው ቃልኪዳን ጋራ የሚመሳሰሉበትንና የሚለያዩበትን ነጥቦች በማነጻጸር ተናገር::
7. ቁጥር 4ትን ስናነብ አብርሃምና ሎጥ አብረው ሲወጡ እናያለን:: በሎጥና በአብርሃም አወጣጥ መካከል የሚታየው ትልቁ ልዩነት ምንድነው?
8. እግዚአብሄር ለአብርሃም የበከነአንን ምድር ርስት አድርጎ እንደሚሰጠው የተናገረው (ቁ7) አብርሃም አገሩን፣ወገኑንና የአባቱን ቤት ትቶ ከወጣ በኋላ መሆኑ ለእኛ የሚያስተምረን ትምህርት ምንድነው?
9. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የማንረዳቸውና የማይገቡን ሃሳቦች ነገር ግን በእምነት ብቻ እንድናደርግ የምንጠየቅባቸውን ጥቂት ነገሮች ዘርዝር::
10. አብርሃም ያሳየውን አይነት የእምነት እርምጃ ዓይነት እንድትወስድ ተጠይቀህ ታውቃለህ ወይ? ከትምህርቱ ያገኘኸውን ነገር ለወገኖችህ አካፍል::

# ጥናት ሁለት (ዕብ 11፡17-19 ዘፍ 22፡1-19)

የጥናት ዓላማ፡- እምነታችን የተመሰረተው በልዑል አምላክ ሁሉን ቻይነትና በእርሱ ባህርይ ላይ እንጂ የፈለግነውን ነገር በማግኘታችንና ባለማግኘታችን ላይ መሆን እንደሌለበት ለመማር፡፡ የምናሰላስለው ጥቅስ፡ «አብርሃም እግዚአብሔር ሙታንን ሊያስነሳ እንደሚችል ተገንዝቦ ነበር፣ ይስሃቅንም ከሞት የመነሳት አምሳያ ሆኖ አገኘው፡፡» ዕብ 11፡19

1. በዘፍ 22፡1-2 ውስጥ አብርሃም እንዲያደርጋቸው የተጠየቃቸውን ነገሮች በሙሉ ዘርዝር፡፡
2. ቁ 3ትን ስታነብ አብርሃም የወሰዳቸው እርምጃዎች ምን ምን ነበሩ?
3. በዚህ ምንባብ ውስጥ አብርሃም በእውነት እግዚአብሄርን ለመታዘዝ ቆርጧል ለማለት የሚያስችሉን ሃሳቦች የትኞቹ ናቸው?
4. በዘፍ 22፡3-11 የምታያቸውን ተዋኖኞች በሙሉ ዘርዝር፡፡ አሽከሮቹ ከአብርሃምና ከይስሃቅ ጋራ አብረው እንዳይሄዱ የወሰነባቸው ምክንያቶች ይሆናሉ ብለህ የምታምንባቸውን ሃሳቦች በሙሉ ዘርዝር፡፡
5. ልጁን ለመሰዋት ሶስት ቀን ሙሉ መጓዙ በአብርሃም ላይ ነገሩን ሊያከብድበት የሚችል ምን ሁኔታ አለ ትላለህ?
6. ይህ ምንባብ ስለ ይስሃቅ የሚነግረን ብዙ ነገር የለም፡፡ በእርጋታ በማንበብ ስለ አብርሃም ልጅ ከክፍሉ ምን ነገሮችን ማየት ትችላለህ?
7. ዕብ 11፡19ን በጥንቃቄ አንብብ፡፡ በዚህ ክፍል መሰረት አብርሃም ልጁ ከሞት እንደሚነሳ አምኗል ወይ? አዎን ካልክ አስረዳ፡፡ ካልሆነ ግን አብርሃም ያመነው ምን ነበረ?
8. አብርሃም ይስሃቅን መልሶ እንደሚያስነሳው አብርሃም በእርግጠኛነት የሚያውቅ ቢሆን ልጁን እንዲሰዋ መጠየቁ ፈተና ይሆን ነበረ ወይ? ለምን?
9. ዕብ 11፡19 ላይ አብርሃምን ስንመለከት እምነቱ ያረፈው በአምላኩ ችሎታ ላይ እንጂ በይስሃቅ መነሳት ላይ እንዳልነበረ ይታያል፡፡ ከዚህ የእምነት ሰው ለህይወትህ የምትማረው ነገር ምንድነው?
10. ከአብርሃም ህይወት የተማርነውን ወደፊት በህይወታችን ተግባራዊ ልናደርግ ስለምንችልባቸው መንገዶች ተወያዩባቸው፡፡

# <u>ጥናት ሶስት (ዕብ 11:24-28)</u>

**የጥናት ዓላማ:- በህይወታችን የሚገጥሙንን አስቸጋሪ ሁኔታዎች ለመጋፈጥ ከፊት ለፊታችን በእምነት የምናየው ተስፋ ሊኖረን እንደሚገባ ለመማር::**

**የምናሰላስለው ጥቅስ: «...ወደፊት የሚቀበለውን ብድራት ከሩቅ ተመልክቷልና::» ዕብ 11:26**

1. **በዕብ 11:24-28 ባለው ምንባብ ውስጥ ሙሴ በእምነት አደረጋቸው የሚላቸውን ሶስት ነገሮች ተናገር::**
2. **ይህንን ክፍል ስናነብ ሙሴ ምርጫዎች እንደነበሩት ይነግረናል:: ሙሴ የነበሩትን የምርጫ ዓይነቶች ዘርዝር:: የእርሱ ምርጫ ምን ሆኖ ተገኘ?**
3. **«ሙሴ ካደገ በኋላ...» ለምንድነው ይህ ክፍል የሙሴን እምነት የተሞላ ውሳኔ ከእድገቱ ጋራ ማያያዝ ያስፈለገው? ይህ ለእኛ ህይወት መንፈሳዊ ትርጉሙ ምንድነው?**
4. **ቁ 25 ላይ «ለጥቂት ጊዜ በሐጥያት ከሚገኝ ደስታ ይልቅ...» ይህንን ሲል ጸሐፊው ሊጠቁመን የፈለገው የትኛውን ደስታ ነው?**
5. **አንድ አማኝ ቁ 25 ትን ብቻ በመመርኮዝ በእርግጠኛነት ደስታንና መከራን በተመለከተ ሊናገር የሚችላቸውን እውነቶች በመዘርዘር ተናገር::**
6. **ሙሴ በዚህ ክፍል የተዘረዘሩትን የእምነት እርምጃዎች ሁሉ ለመውሰድ እንዲደፍር ያስቻለው ነገር ምንድነው? «ወደፊት የሚቀበለው ብድራት» በመባል የሰፈረው ምን እንደሆነ የእግዚአብሄርን ቃል በመመርኮዝ አስረዳ::**
7. **ቁ 27 ላይ «የማይታየውንም እንዳየው አድርጎ...» ሲል፣ የማይታየው ነገር ግን ሙሴ ሊያይ የቻለው ነገር ምን ነበረ?**
8. **ከቀሳፊው መልአክ ለመዳን የእስራኤል ልጆች በሙሉ ፋሲካን እንዳደረጉ እናውቃለን:: ነገር ግን ስለ ሙሴ «...ፋሲካን በእምነት አደረገ::» ይላል:: የእርሱ ድርጊት ተለይቶ ለምን በእምነት በመባል ትኩረት የተሰጠው ይመስልሃል?**
9. **በቁ 26 ላይ «ተመልክቷል» በቁ 27 ደግሞ «የማይታየውን እንዳየው በመቁጠር» ይላል:: በሁለቱም በሥጋ ዓይን የማይታየውን አይቶ ነበረ:: አንተስ ዛሬ የምታልፍባቸውን አስቸጋሪ ሁኔታዎች ለመጋፈጥ የሚያስችልህ ከፊትህ በእምነት የምታየው ነገር ምንድነው? ከክፍሉ የተማርከውና በውስጥህ የቀረ ነገር ካለ ለወገኖች አካፍል::**

# ጥናት አራት (ዕብ 11:30 ኢያሱ 6:1-21 )

የጥናት ዓላማ:- ምን ጊዜም ቢሆን እምነትን እምነት የሚያሰኘው እግዚአብሄር በተናገረው ነገር ላይ መመስረቱ እንደሆነ ለመማር::

የምናሰላስለው ጥቅስ: «እግዚአብሄር ይህችን ከተማ ሰጥቷችኋልና ጩኹ!» ኢያሱ 6:16

1. በቁ 2-5 ላይ እግዚአብሄር ኢያሪኮ የምትፈርስበትን ለኢያሱና ለህዝቡ የሰጣቸውን መመሪያ በቅደም ተከተል ዘርዝር::
2. ኢያሪኮን ለማፍረስ የወሰደው ቀናት ስንት ነበረ? ከተማይቱን ለማፍረስ የእስራኤል ልጆች በአጠቃላይ ስንት ጊዜ መዞር ነበረባቸው?
3. ከተማይቱን ለማፍረስ እግዚአብሄር ተጠቀመ ብለን መዘርዘር ብንጀምር ማን ማንን መጥቀስ እንችላለን?
4. በቁ 16 ላይ የሰፈረውን ኢያሱ ለህዝቡ በሙሉ የተናገረውን ቃል ተመልክተን ኢያሱ እምነት አለው ማለት የሚያስችለን ነገር ምንድነው? ቁ 2ትን ተመልከት
5. «ለእግዚአብሄር የተቀደሰ ስለሆነ...» የሚለው በቁ 19 ላይ የሰፈረው ሃሳብ ምን ማለቱ እንደሆነ ነው የምትረዳው?
6. ኢያሪኮን ያፈረሰው የመለከቱ መነፋት ነው ወይስ የህዝቡ ጩኸት? ቁ5 ና ቁ20 እግዚአብሄር ያዘዘውን ትዕዛዝና ህዝቡ በተግባር ያዋሉትን በማነጻጸር ተናገር::
7. የእስራኤል ልጆች በየቀኑ እየተነሱ ከተማይቱን ሲዞሩና ይህንንም እለት እለት ፈጽመው ወደ ካምፓቸው ሲመለሱ በአዕምሯቸው የሚመላለሰው ሀሳብ ምን ይመስልሃል?
8. «እግዚአብሄር ይህችን ከተማ ሰጥቷችኋል...» ቁ 16 በማለት ኢያሱ በድፍረት እንዲናገር ያስቻለው ነገር ምንድነው? አንድ አማኝ ይህንን ጥቅስ ተጠቅሞ እግዚአብሄር እንደሰጠው አድርጎ መዝመት ይችላል ወይ? ለምን?
9. እግዚአብሄር ቃል ገብቶልህ/ተናግሮህ ያውቃል ወይ? ላንተ የተናገረህንና የኢያሱን በማነጻጸር የምታየውን ተመሳሳይነት እንዲሁም ልዩነቱን አስረዳ:: እግዚአብሄር የተናገረው ከሚያልፍ ሰማይና ምድር ቢያልፍ ይቀለዋልና ብንታመነው አያሳፍረንም::

# ጥናት አምስት (ዕብ 11:31 ኢያሱ 2:1-24 )

**የጥናት ዓላማ፡- የምናውቀውንና የምንችለውን ማድረጋችን እምነት የማጣት ምልክት እንዳልሆነ ለመማር::**

**የምናሰላስለው ጥቅስ: «..ወደምሰጣቸው ምድር ለመግባት የዮርዳኖስን ወንዝ ተሻገሩ» ኢያሱ1:2**
**«ሄዳችሁ ምድሪቱን፤ በተለይም የኢያሪኮን ከተማ ሰልሉ» ኢያሱ 2:1**

1. **በምዕ አንድ ላይ ለህዝቡ የሚፈለገውን ነገር ከተናገረ በኋላ ኢያሱ የወሰደው የመጀመሪያ እርምጃ ምን ነበረ? በዘኁ 13 የተላኩት ሰላዮች ከነዚህ ሰላዮች የሚለዩባቸውን ቢያንስ ሶስት ነገሮች ተናገር::**
2. **ኢያሱ በሰላይነት ሄዶ ምድሪቱን እንደሰለለ እናውቃለን:: ለምንድነው ታዲያ ተጨማሪ ሰላይ መላክ ያስፈለገው?**
3. **በቁ 1-7 መሰረት ረዓብ ወደ ቤትዋ ለገቡት ሰላዮች ያደረገችው ምን ነበረ? ከንጉሱ የደረሳት መልዕክትስ ምን ነበረ? የረአብን ድርጊትና የሰጠችውን ምላሽ ከንጉሱ ጥያቄ ጋራ እንዴት ታየዋለህ?**
4. **በቁ 8-11 ረዓብ «አውቃለሁ» በማለት ለሰላዮቹ የነገረቻቸው ሶስት እውነቶችን ተናገር:: ስለ ኢያሪኮ ህዝብ የሰጠቻቸው ጠቃሚ መረጃዎች ምን እንደ ነበሩ ተናገር:: ይህን ሁሉ መረጃ መኖሩ ለረአብ ውሳኔ ምን አስተዋጽያ አድርጓል ታምናለህ?**
5. **ዕብ 11:31 ረአብ ሰላዮቹን በእምነት ተቀበለች ያለበት ምክንያት ከምን ተነስቶ ነው?**
6. **ረአብ ብቻ ሳትሆን የተላኩትም ሰላዮቹ እምነት ያላቸው ሰዎች መሆናቸውን ቁ 14 በምን መንገድ ነው የሚያሳየን?**
7. **ሰላዩቹ በቁ 17-21 ባለው ክፍል ውስጥ መሃላቸው ስለሚጸናበት ሁኔታ የተናገሯቸው ነጥቦች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር::**
8. **በዘኁ 13:26 እና በኢያሱ 2:23 መካከል የሚታይህ አንድ ጉልህ የሆነ ልዩነት ምንድነው?**
9. **እግዚአብሄር ምድሪቱን እንደሚሰጣቸው ደጋግሞ ተናግሯቸዋል:: ታዲያ ሰላይ መላክ እግዚአብሄርን አለማመን ሆኖ አይቆጠርም ወይ?**
10. **እግዚአብሄር በህይወትህ እንደሚያደርገው ለተናገረህ ነገር በአንተ በኩል ምን ያህል ዝግጅት አድርገሃል?**

# <u>ጥናት ስድስት (ዕብ 11:32-40)</u>

የጥናት ዓላማ:- እምነት የምንፈልገውን ነገር የምናገኝበት መሳሪያ ሳይሆን እግዚአብሄር የተናገረውን እንደሚያደርግ በማመን የሚያስከፍለው ነገር እንኳን ቢኖር ለመክፈል ዝግጁ መሆን መሆኑን ለመማር::

የምናሰላስለው ጥቅስ: «ሌሎቹ ደግሞ የተሻለውን ትንሳኤ ለማግኘት ሲሉ መትረፍን ንቀው ለሞት ለሚዳርግ ሥቃይ ራሳቸውን ሰጡ፤» ዕብ 11:35

1. ይህ ክፍል ገና የሚጀምረው «እንግዲህ ከዚህ በላይ ምን ልበል?» በማለት ነው:: ከጸሐፊው አባባል የምትረዳው ነገር ምንድነው?
2. በቁ 32 ላይ የተጠቀሱት የብሉይ ኪዳን ሰዎች በሙሉ በጋራ ያላቸው አንድ ነገር ምንድነው? በዚህ ዝርዝር ውስጥ መግባቱ የሚያስገርምህ ሰው አለ ወይ? አለ ካልክ የትኛው እንደሆነ ተናገር::
3. በቁ 32 እንደምናየው መሳፍንት፤ነገስታት፤ካህናት፤ነብያት ሁሉ አገልግሎታቸውን በእምነት ስላከናወኑ በእምነት ጀግኖች ውስጥ እንደሰፈሩ እንመለከታለን:: ይህ ለእኛ የሚያስተምረን ነገር ምንድነው?
4. በቁ 33 ላይ «እነዚህ» በማለት የጠቀሳቸው ሰዎች ያሳለፉት ልምምድና በቁ 35 ላይ «ሌሎቹ» በማለት የጠቀሳቸው ያሳለፉት ልምምድ ልዩነት ምን እንደሆነ አስረዳ:: በተለይ የኋለኞቹ ያለፉበትን በግልጽ መናገሩ ሰዎች ወደ ጌታ እንዳይመጡ አያደርግም ወይ?
5. በቁ 35-38 ላይ የሰፈሩት ተሸናፊ መስለው የሚታዩ ሰዎች ለምንድነው የእምነት ጀግኖች ተብለው ከሚጠሩት ጋራ ስማቸው እንዲሰፍር የሆነው? እነዚህን ሰዎች የእምነት ሰዎች ሊያሰኛቸው የቻለው ነገር ምኑ ነው?
6. ጸሃፊው ከአቤል ጀምሮ ያሉትን የእምነት ጀግኖች በመዘርዘር እኛ እንድንማረው የፈለገው ዋነኛ ትምህርት ምንድነው? እኛን ከነዚህ ሰዎች በበለጠ በእምነት ልያራምዱን የሚያስችሉን ምክንያቶች አሉ ብለህ ታምናለህ ወይ? አሉ ካልክ ዘርዝራቸው::
7. ቁ 39-40ን በድጋሚ አንብቡና ጸሐፊው ምን ለማለት እንደፈለገ ተወያዩበት::
8. በዚህ ክፍል የምትመለከተውን በተለይም በቁ 35-38 ላይ የሰፈረውን ሃሳብ ስለ እምነት ካለህ አመለካከት ጋራ እንዴት ታነጻጽረዋለህ? ይህንን ክፍል መማርህ እምነት የሚለውን ሃሳብ በተመለከተ ምን የተለየ ሃሳብ እንደተማርክ ለወገኖችህ አካፍል::

# ጥናት ሰባት (ዕብ 11:23 ዘፍ ዘጸ 1:15-2:10)

የጥናት ዓላማ:- ከፊታችን ሊሆን ያለውን ነገር ባናውቅም እንኳን እንደሙሴ ቤተሰቦች በየተረዳነው መኖር ስንጀምር እርሱ ስራውን እንደሚሰራ ለመማር::
የምናሰላስለው ጥቅስ: «ሙሴ ከተወለደ በኋላ ወላጆቹ መልከ ምልካም መሆኑን ስላዩ በእምነት ሶስት ወር ሸሸጉት፣ የንጉሱንም ዓዋጅ አልፈሩም::» ዕብ 11:23

1. ዘጸ 1:15-2:10 የሰፈረውን ሃሳብ በራስህ ቋንቋ ታሪኩን ለወገኖች ተናገር::
2. ዘጸ 1:15-22 ትን ስታነብ የእብራውያንን ወንዶች ልጆች እንዲገድሉ ከፈርዖን ትዕዛዝን የተቀበሉት ምን ያህል ሰዎች ነበሩ?
3. ትዕዛዝ የተቀበሉትን ሰዎች ብዛት በማየት የሙሴ ቤተሰቦች የወሰዱትን እርምጃ ላለመውሰድ ምክንያት አድርገው ማቅረብ የሚችሏቸው ምን ነገሮች ይታዩሃል?
4. መደበቅ ከሚችሉበት ደረጃ ሲያልፍ ማለትም ከሶስት ወር በኋላ ቤተስቦቹ በ2:3-4 መሰረት የወሰዷቸውን እርምጃዎች በቅደም ተከተል ተናገር::
5. በዚህ ታሪክ ውስጥ የሙሴ እህት የተጫወተችው ሚና ምን ነበረ?
6. የሙሴ ቤተሰቦች የወሰዷቸውን እርምጃዎች ስንመለከት ከቁ 5-10 ደግሞ እግዚአብሄር የሰራውን እንመለከታለን:: ከዚህ ስለሰውና ስለ እግዚአብሄር ድርሻ ምን ትማራለህ?
7. ዕብ 11:23 «በእምነት ሶስት ወር ሸሸጉት» ይላል:: የሙሴ ቤተሰቦች ያደረጉትን ድርጊት እምነት የሚያሰኘው ነገር ምንድነው?
8. የሙሴ ቤተሰቦች ሙሴ ለፈርዖን የልጅ ልጅ እንደሚሆን አስቀድመው አያውቁም:: ታዲያ ይህንን ያህል ህይወታቸውን ሊጠይቅ የሚችለውን ውሳኔ እንዴት ሊወስኑ ቻሉ?
9. እግዚአብሄር የነገሮችን አቅጣጫ አስቀድሞ ቢያሳይህ፤ በከባድ ሁኔታዎች ውስጥም ቢሆን ለመታዘዝ ምን ያህል ይረዳህ ይመስልሃል? የሙሴ ቤተሰቦች የልጃቸውን የህይወት አቅጣጫ ሳያውቁ ለመታዘዝ መጨከናቸው ምን ያስተምርሃል?
10. ሁኔታዎች የሚሄዱበትን ካወቁ በኋላ መታዘዝ እምነት ስላልሆነ የሙሴን ወላጆች አይነት ሳያዩ የመታዘዝን እምነት ለማዳበር ልብህ ምን ያህል ቆርጧል?

    እምነት በዘመናችን ሲሰጠው የሚታየው ትርጉም መጽሐፍ ቅዱሳችን እምነት ከሚለው ሃሳብ ጋራ ተቃራኒና አብሮ የማይሄድ እንግዳ ነገር መሆኑን ለማስተዋል ብዙ ሩቅ መሄድ ሳያስፈልገን በቴሌቭዥናችን ሆኖ ቤታችን ድረስ በተለያየ መልኩ ይመጣልናል::